# ምነው ኖርዌይ!?

ወለላዬ ከስዊድን welelaye2@yahoo.com

ሀገራችን በግፍ ችንካር ተከንቸራ፤
በሞት ሸረት ተውጥራ፤
የመከራ የጭንቅ ማቅ፤
ተከናንባ ስትማቅቅ፤
ከግፈኞች መዳፍ ወጥተን፤
ባንቺ ጉያ ተወሽቀን፤
ግዜ ባማጥን ቀን በገፋን፤
ምነው! ምነው! ምነው! ኖርዌይ ምነው! አስሎ?
ችግራችን ታየሽ ቀሎ።

ምን አጥፍተን ጨከንሽብን፤
ምነው ፊትሽ ጠቆረብን፤
ምነው ጣልሽን ከእቅፍሽ፤
ምን አረግን ምን በደልንሽ?
ደራሽ ሆነሽ ለተጎዳ፤
አግኝተሽን ባንችው ጓዳ፤
ምነው ውጪ ወረወርሽን፤
በምን ጥፋት ተቀየምሽን?

ምነው! ምነው! ምነው ኖርዌ ምነው! አስሎ?
ችግራችን ታየሽ ቀሎ?
ምነው አስሎ ምነው ኖርዌ፤
ሀገራችን የዘር ደዌ፤
ይዟት ታማ ስትማቅቅ፤
በችግሯ ስትጨነቅ፤
የሰው ክብር ሰብዓዊነት፤
ዲሞክራሲ እኩልነት፤
ጭራሽ አጥታ ቆማ እራቁት፤
ሕግ ጠፍቶ ፍርድ ሲጎድል፤
ባንቺ ጉያ ብንጠለል፤
ጉዳጉዱን በጠረግን፤
ስርቻውን ባጣጠብን፤
ምን አጥፍተን ምን በድለን፤
ፀዳል ፊትሽ ጠቆረብን።

ጉያሽ ኖረን ለብዙ ዓመት፤
ሳንጨብጥ ትንሽ ቅሪት፤
ካንቺው ወስደን፤
ላንቺው ሰጥተን፤
አጎብሰን አንገት ደፍተን፤
ግብር ከፍለን ሕግ አክብረን፤
አለበደል አለጥፋት፤
በኖርንብሽ በመዋተት፤

ምነው! ኖርዌ ምነው? አስሎ፤
ችግራችን ታየሽ ቀሎ?
ደጅሽ ተርፎ ተትረፍርፎ፤
እጅግ በዝቶ ሀብትሽ ገዝፎ፤
ሆነሽ ሳለሽ ሀብታም ምድር፤
ምነው? ጣልሽን እኛን ለአሳር?

ሲቸግረው ሰው ሲከፋ፤
በሀገሩ ሲያጣ ተስፋ፤
ሁሉም ቢሆን ይሰደዳል፤
ዛሬም አለ ፊትም ደርሷል።
ሆኖም ወጥቶ ለሚጠለል፤
የታላቁ መጽሐፍ ቃል፤
ድጋፍህን ስጠው እንዲል ...
እያወቅሽው እያስተማርሽ፤
በዓለም ዙሪያ እየሰበክሽ፤
ሰብዓዊ ሀገር ጥሩ እያሉሽ፤
ምነው በእኛ እንዲህ ጨከንሽ?

ምነው! ምነው! ምነው! ኖርዌ ምነው! አስሎ፤
ችግራችን ታየሽ ቀሎ?

ወለላዬ ከስዊድን welelaye2@yahoo.com
በኖርዌይ እንግልትና ችግር ለደረሰባቸው
ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች መታሰቢያ ይሁን!

Designed by EZ